## I.

በስመ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ። እጽሕፍ ፡ የኢሮብ ፡ ትውልድ ፡ ታሪክ ።

እኔ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ አላበዘንኍም ። ለብዞች ፡ ባላገሮች ፡ ታሪኩን ፡ እናውቃለን ፡ ለሚሉ[1] ፡ ሁሉ ፡ ጠየቅኍ ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ብጠይቅ ፡ አንድ ፡ ታሪክ ፡ ያመጣል ፤ አንድ ፡ ብጠይቅም ፡ ሌላ ፡ ታሪክ ፡ ያመጣል ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቤ ፡ እኒያ ፡ የሚበዙ ፡ ምልክት ፡ እያሰጡ ፡ የሚተርኩትን ፡ ተርታንና ፡ ታሪኩን ፡ ሁሉ ፡ ጀምሬ ፡ መጣፍ ፡ ጀመርኩ ።

እሳቸው ፡ መጀመርያው ፡ ማለት ፡ ፊተኛው ፡ አባታችን ፡ ከኢሮፓ ፡ ነው ፡ የመጣ ፡ ይሉታል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኢሮብ ፡ ተባልን ፡ እያሉ ፡ ይተርካሉ ።

### ፩ኛ ፡ ክፍል ።

ሐፀይ ፡ ይትባረክ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ሸፍቶ ፡ በአጋሜ ፡ በረኻ ፡ ይኖር ፡ ነበረ ። የአጋሜ ፡ ትልቅ ፡ ገዳም ፡ ጕንድጕንደ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ገዳም ፡ አንድ ፡ መነኵሴ ፡ ነበሩ ፤ የምሽታቸው ፡ አገር ፡ ጕንድጕንደ ፡ ነበረ ፡ የሳቸው ፡ አገር ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ነበረ ። እኚህ ፡ መነኵሴ ፡ አንዲት ፡ ልጅ ፡ ወለዱ ። ይህች ፡ የግርዋና ፡ የጅዋ ፡ ጣት ፡ ፳፬ነበረ ። አባትዋና ፡ እናትዋ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ኢያሉ ፡ ሲገረሙ ፡ ነበሩ ። ሲሉ ፡ ሲሉ ፡ ወደ ፡ ጠንቋይ ፡ እንውሰዳት ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ጠንቋይ ፡ ምሥጢሩዋን ፡ ሊፈታላቸው ፡ ይዘዋት ፡ ሄዱ ። ጠንቋይም ፡ ተስዋ ፡ የሚወለድ ፡ ላባቱ ፡ ወገን ፡ የሚያነግሥ ፡ ለናቱ ፡ ወገን ፡ የሚያጠፋ ፡ ነው ፡

ብሎ ፡ ጠንቈለላቸው ። እናትዋና ፡ አባትዋ ፡ ለወንድ ፡ እንሰጣ
ት ፡ በሰርቅም ፡ እንዳትወልድ ፡ በመልክም ፡ እንጠብቃት ፡ ተቤ
ትም ፡ አናውጣት ፡ ብለው ፡ በብርቱ ፡ ሲጠብቁዋት ፡ ነበሩ ። ሐ
ፀይ ፡ ይትብረክ ፡ በበረኻ ፡ ሽፍቶ ፡ ሣለ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሥማ ፤
ዮት ፡ ላገኛት ፡ ነኝ ፡ ኢያለ ፡ ከወታደሮቹ ፡ የታመኑትን ፡ እየሰ
ደደ ፡ ምናልባች ፡ በረኻ ፡ ብትወጣ ፡ ቶሎ ፡ ብላችኍ ፡ ላኩልኝ ፡
ኢያለ ፡ ይሰዳቸው ፡ ነበረ ። ወታደሮች ፡ ሲጠብቁ ፡ ሲጠብቁ ፡
አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ውኃ ፡ ልትቀዳ ፡ ወረደች ። አንዳ
ንድ ፡ እንጨት ፡ ልትለቅም ፡ በረኻ ፡ ወጥታ ፡ ሣለች ፡ ነው ፡ ብ
ለው ፡ ይተርካሉ ። ወታደሮችም ፡ ለጌታቸው ፡ ቶሎ ፡ ብለህ ፡ ና ፡
አገኘሃት ፡ አጣሃት ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ላኩለት ። እሱም ፡ ይ
ህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ መጣ ፡ ወደ ፡ ቤትዋ ፡ ስትመ
ለስ ፡ ሣለች ፡ አገኛት ፤ ተሱም ፡ ርግዝና ፡ አስቀረች ።

ርግዝናዋ ፡ ከታወቀ ፡ ወዲያ ፡ የናትዋ ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡
ተሰብስበው ፡ እንግደላት ፡ ብለው ፡ መከሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ትልል
ቆች ፡ ከስዋ ፡ የተወለደን ፡ እንግደል ፡ እንጂ ፡ እያየች ፡ እንዴ
ት ፡ ብለን ፡ እንገድላታለን ፡ ብለው ፡ መከሩ ። ይህን ፡ ሲመክሩ ፡
ሣሉ ፡ አንዲት ፡ ወዳጅዋ ፡ አሽከር ፡ ሰማቻቸው ፤ ሰምታም ፡ ቶ
ሎ ፡ ብላ ፡ ሂዲ ፡ ነገረቻት ። ሁለታቸው ፡ ተማከረው ፡ አንድ ፡ (*sic*)
አገልግል ፡ ሰፉ ፡ በውስጡ ፡ ቅጥራን ፡ ለበጡት ። ያችም ፡ ወለ
ደች ። የተወለደውም ፡ ተባት ፡ ሆነ ፡ መልኩም ፡ ውብ ፡ ነበረ ።
እንደ ፡ እናቱ ፡ የጁና ፡ የግሩ ፡ ጣቶች ፡ ፳፬ነበሩ ። በተሰፋው ፡
አገልግል ፡ ውስጥ ፡ አርገው ፡ ፪ቸው ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ጣሉት ፡
ጥለውት ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ሣሉ ፡ እናቲቱ ፡ ፪ቱ ፡
ዓይንዋን ፡ ታወረች ። በጕንድጕንደም ፡ መነኵሴ ፡ ሁና ፡ ትኖር ፡
ነበረች ።

ያ ፡ አሽከር ፡ በዚያ ፡ ወንዝ ፡ ተጥሎ ፡ ሣለ ፡ ነጋዴ ፡ መጡ ።
አገልግሉን ፡ አንስተው ፡ ቢከፍቱት ፡ ይህን ፡ ውብ ፡ ልጅ ፡ አዩ ።